የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

ቁ/መ/ቁ፡- 263422
ጥቅምት 03 ቀን 2018 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ሽመክት አሰፋ

በዕውቀት በላይ

መላኩ ካሳዬ

ማርታ ተካ

አመልካች፡- አቶ መልካሙ ብርሃኑ — ቀርቧል

ተጠሪ፡- ኮለፌ ቀራንዩ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት አስተዳደር ጽ/ቤት ጠፍቷል

መዝገቡን በክረምት ወቅት ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሚያዝያ 14 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 135496፤ በቀን 30/10/2015ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 312040፤ በቀን 30/7/2016ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የከተማ ይዞታን በሚመለከት የቀረበን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ፤ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሰረተው ክስ ይዘቱ፡- በኮለፌ ቀራንዩ ክ/ከተማ ቤቴል ሚካኤል ተብሎ በሚጠራው ክልል ልዩ ቦታው ማርያም ትርዳው ተብሎ በሚጠራ አካባቢ የሚገኝ አዋሳኙ በምስራቅ መንገድ፤ በምእራብ መንገድ፤ በሰሜን መንገድ እና በደቡብ አቶ መስፍን ኪዳኔ የሚያዋስነው ስፋቱ 210 ካ/ሜ የሆነ በኮድ 198 ተመዝግቦ ወደ መሬት ባንክ የገባ የመንግስት ይዞታ ሆኖ እያለ አመልካች በወረራ መያዛቸውን፤ ይዞታው በ1997 እና 2003ዓ/ም በተነሳው የመስመር ካርታ አመልካች ስለመሆኑም ሆነ በይዞታው ላይ በወቅቱ ግንባታ የነበረው ስለመሆኑ የሚገልጽ ነገር የለም፤ አመልካች በህገወጥ መንገድ ስልጣን ባለው የፍ/ቤቱን አዋጅ ሳያገኙ በወረራ ስለያዙ ይለቁልኝ በማለት ጥያቄ ያቀረበ መሬት ባንክ የገባ የመንግስት ቦታ ነው በማለት እንዲወሰንልን እንዲሁም ያለግ[illegible]

Scan Me
Scan Me
Federal Supreme Court
Federal Democratic Republic of Ethiopia
M26T
ሰበር ችሎት
Scan Me
2:11 pm 05/
CamScanner

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

ለ/መ/ቁ፡- 263422
ጥቅምት 03 ቀን 2018 ዓ/ም

በያዙት ላይ የገነቡት ግንባታ በማፍረስ ይዞታው እንዲያስረክቡ ይወሰንላቸው በንድ ጻኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው።

አመልካች ለክሱ በለጡት መልስ የተጠሪ ክስ የክስ ምክንያት የለውም፣ ጉዳዩ ከዚህ ቀደም በመ/ቁ 289197 ላይ ተከራክረን በፍርድ ያለቀ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 5 መሰረት በድጋሚ ክስ ሊቀርብ አይገባም፣ ክሱ በደረጃ የሚቋረጥ ነው የሚሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም በፍሬጉዳይ መልሳቸውም ተጠሪ አመልካች ባዶ መሬት በመውረር ህገወጥ ግንባታ ገንብቷል በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተገቢነት የሌለው መሆኑን፣ አመልካች በክሱ የተጠቀሰው ይዞታ መሬት ከ1994ዓ/ም ጀምሮ በመያዝ ግንባታ ገንብቼ ስጠቀምበት የቆየሁ ይዞታ መሆኑን፣ በፌደራል መመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 289197 በዚሁ ይዞታ ጋር በተያያዘ ኮልፌ ቀራንዩ ክ/ከተማ ወረዳ 07 ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ጋር የሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርቤ ተከራክረን ይህው አሁን ክርክር ያስነሳው ይዞታ በ1997ዓ/ም አየር እና መስመር ካርታ ላይ ግንባታው ይታይ የነበረ ስለመሆኑ ፍ/ቤቱ ባደረገው ማጣራት ከክፍለከተማው የመሬት ይዞታ አስተዳደር እና ልማት ጽ/ቤት በቁጥር ኮ/ቁ/የመ/ይ/ለ/ማሶ/ገ/ስራሂደት 3454/13፣ በቀን 03/06/2013ዓ.ም በሰጠው ምላሽ ካረጋገጠ በኃላ አከራካሪው ይዞታ በአመልካች እጅ የነበረ እና በይዞታው ላይ ግንባታ የነበረው ስለመሆኑ የነበረው ግንባታ የኮልፌ ቀራንዩ ክ/ከተማ ወረዳ 07 ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ማፍረሱን ተረጋግጦ በይዞታዉ ላይ የፈጠረው ሁከት እንዲወገድ እና ደንብ ማስከበሩ ያፈረሰው ግንባታዉ ወደነበረበት እንዲመልስ ተወስኗል፣ ተጠሪ አመልካች በዚሁ ይዞታ ላይ ያለግንባታ ፈቃድ ግንባታ ገንብቷል በሚል ቢከራከርም በይዞታው ላይ የገነባሁት ቤት ከ1997ዓ/ም በፊት የተሰራ ሲሆን የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ ህግና መመሪያ የወጣው ከ1997ዓ/ም በኃላ በመሆኑ የተጠሪ ክርክር ተቀባይነት የለውም፣ በመሆኑም ክርክር ያስነሳው ይዞታ የአመልካች በመሆኑ ይዞታው ላይ በህገወጥ መንገድ የገነባው ግንባታ የለም ተብሎ እንዲወሰንልኝ በሚል ተከራክረዋል።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ክሱን ሰምቶ በአመልካች በኩል የተነሱት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያች ውስጥ አመልካች ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው በሚል ያነሱት መቃወሚያ አስቀድሞ በመ/ቁ 28917 ላይ የነበረው ክርክር ሁከት ይወገድልኝ የሚመለከት ሲሆን ተጠሪ አሁን ያቀረቡት ክስ ደግሞ ባለቤትነት መፋለም የሚመለከት በመሆኑ በቀደመው ክርክር የቀረበው የስረ-ነገር ክርክርና የተያዘው ጭብጥ አዲስ ከቀረበው ክስ ጋር የስረ-ነገር ክርክርና ጭብጥ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ባለመሆኑ ከዚህ በፊት ፍርድ ያለቀ ጉዳይ ነው ሊባል የሚችል አደለም በማለት ቀሪዎች የተነሱት መቃወሚያች ውድቅ በማድረግ በፍሬጉዳይ ላይ የቀረበው ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ለክርክር መነሻ የሆነው ስፋቱ 210ካ/ሜ የሆነው ይዞታ ኮድ ተሰጥቶት መሬት ባንክ የገባ የመንግስት ይዞታ በመሆኑ አመልካች ለቀው ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል።

አመልካች በሰር ፍ/ቤት ያነሱት የመጀመሪያ ደረጃ [illegible] ይዞታው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የፍ/ቤቱ ውሳኔ ይግባኝ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ [illegible] ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ያጸድቅባቸዋል የፍ/ቤቱ አግባብነት ያለው ሲሆን ጉዳዩ ከዚህ በፊት በፍርድ [illegible] መሆኑ ለአግባቡ ተጣርቷል ወ[illegible]

Scan Me
Scan Me
Scan Me

2:11 pm 05

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

ለ/መ/ቁ፡- 263422
ጥቅምት 03 ቀን 2018 ዓ/ም

ሟቹ ይዞ በጉዳዩ ላይ ግራቀኙን አከራክሮ ሲወስን አስቀድሞ በመ/ቁ 28917 የነበረው ክርክር ሁከት ይጠገድልኝ የሚመለከት ሲሆን የተጠሪ አሁን ያቀረበው ክስ መፋለም የሚመለከት በመሆኑ በሁለቱም ጉዳዮች የተያዘው ጭብጥም ሆነ ፍሬጉዳዩ የተለያየ በመሆኑ በፍርድ ያለቀ ነው ሊባል አይችልም በሚል ስር ፍርድ ቤት በአመልካች የተነሳው መቃወሚያ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ መሆኑን ጠቅሶ እንደአጠቃላይ አመልካች ክርክር ያሰነሳው ይዞታ ከ1994ዓ.ም ጀምሮ የያዝኩት ይዞታዬ ነው በሚል ቢከራከርም አመልካች አርሶአደር እንዳልሆነ በማስረጃ መረጋገጡን፤የከተማ ቦታ ማግኘት የሚቻለው በሊዝ ስርአት ብቻ ሲሆን አመልካች በሊዝ ስለማግኘታቸውም ሆነ በሰነድአልባ ይዞታዎች መስተንግዶ በመመሪያ ቁጥር 18/2006 አንቀጽ 5 መሰረት ይዞታው ላይ መብት ያገኘ ስለመሆኑም ሆነ ከ20 አመት በላይ ይዞታው ይዞ ስለመቆየቱ የሚረጋግጥ ያቀረበው ማስረጃ የለም፤ ክርክር ያስነሳው ይዞታ ኮድ ቁጥር 198 በመስጠት መሬት ባንክ የገባ የመንግስት ይዞታ ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል በተደረገው ማጣራት ሊረጋገጥ መቻሉን ጠቅሶ አመልካች ይዞታው ለቆ ለተጠሪ ያስረክብ በሚል በስር መወሰኑ ተገቢ ነው በማለት የስር ፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ በማጽናት በመ/ቁ 312040፤ በቀን 30/7/2016ዓ.ም ወስኗል።

አመልካች ሚያዝያ 14 ቀን 2016 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም- ከመነሻውም የተጠሪ ክስ በፍ/ቤት ቀርቦ ዳኝነት የሚሰጥበት አደለም በሚል በስር ፍ/ቤቶች ያቀረብኩት ክርክር ውድቅ መደረጉ ተገቢ አደለም፤ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ሆኖ እያለ ከዚህ ቀደም በመ/ቁ 289197 ከወረዳ 07 ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት ጋር በነበረን የሁከት ይወገድልኝ ክርክር ፍ/ቤቱ አመልካች ይህው ይዞታ በምን አግባብ እንደያገኙት፤ መሬቱ በ1997ዓ/ም እና በ2003ዓ/ም የመስመር ካርታ ላይ የሚታይ ግንባታ ነበረ መሆን አለመሆኑ፤ መሬት ባንክ መግባት አለመግባቱ የአሁኑ ተጠሪ አጣርቶ ምላሽ እንዲሰጥ ትእዛዝ ተሰጥቶ የአሁኑ ተጠሪ ለፍ/ቤቱ በላከው ምላሽ ይዞታው በ1997ዓ/ም በተነሳ አየር ካርታ ላይ በስሜ ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን ነገር ግን እላዩ ላይ ያለው ቤት በወረዳው ደንብ ማስከበር ስለመፈረሰ ቤቱ አይታይም በሚል ምላሽ መስጠቱን ተከትሎ ፍ/ቤቱ ይዞታው የአመልካች መሆኑና መሬት ባንክ ገብቶ የማያውቅ መሆኑን አረጋግጦ መወሰኑ ተረጋግጦ እያለ አንድን ጉዳይ በፍርድ ያለቀ ነው ሊባል የሚችለው ተመሳሳይ ጭብጥ ስለመኖሩ ሊረጋገጥ እንጂ ተመሳሳይ የክስ ምክንያት ሲኖረው እንዳልሆነ እየታወቀ፤ ቀድሞ በነበረው ክርክር የተነሳው ፍሬነገር እና ጭብጥ አሁን ከተነሳው የፍሬነገር ጭብጥ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ እያለ ቀድሞ በነበረው ክርክረም ሆነ በዚህ ጉዳይ ዋናው የክርክር ጭብጥ አመልካች ይዞታው በምን አግባብ ሊይዝ ቻለ፤ ይዞታው በ1997ዓ/ም አየር ካርታ በማን ስም ተመዝግቧል፤ ይዞታው መሬት ባንክ ገብቷል ወይስ አልገባም የሚል ስለሆነ ጭብጦቹ ተመሳሳይ እስከሆኑ ድረስ ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ አልቋል በሚል ያነሳሁት መቃወሚያ ተገቢ ሆኖ እያለ ስር ፍርድ [illegible] መቃወሚያዬን አለመቀበላቸው ተገቢ አደለም፤ መሬት [illegible] ይዞታው በይርጋ ሊታገድ አይችልም በሚል [illegible] ጉዳዩ የመሬት ባንክ ገብቶ የማያውቅ መሆኑን ከአስረጂ ጋር ያቀረበ ሲሆን ስለማይችል ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባ ነበር በማለት ባላጣበት ጉዳዩ የመፋለም ክርክር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

ሰ/መ/ቁ፡- 263422
ኅዳር 03 ቀን 2018 ዓ/ም

ያነሳሁዋቸው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ውድቅ መደረጋቸው ስህተት ነው፤ በፍሬጉዳይ ላይ አከራክረው የሰጡት ውሳኔ የማስረዳ ምክና መርህን ያልተከተለ በመሆኑ የሰር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የሰበር ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ክርክር ያስነሳው ይዞታ አስመልክቶ አስቀድሞ በመ/ቁ 289197 ግራቀኙ ተከራክረው ይዞታው በአየር ካርታ ላይ የሚታይና አመልካች በስነድ አልባነት ሊስተናገድበት የሚችል መሆኑ ተረጋግጦ የተጠሪ ተግባር ሁከት በመሆኑ ሁከቱ እንዲወገድ ውሳኔ በተሰጠበት ሁኔታ አሁን የቀረበው ክስ ርእሱ መፋለም ነው ከመባሉ ውጪ በፍሬጉዳዩ ላይ በጭብጥነት የተጣሩት ተመሳሳይ በሆነበት ሁኔታ አመልካች አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው በማለት ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሀ.ቁ 5(1) ድንጋጌ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 130410፤ 229870 እና በሌሎች መዛግብት ከሰጠው ገዢ ትርጉም አንጻር ከመመርመር በሚል ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል።

ተጠሪ የካቲት 28 ቀን 2017 ዓ.ም የሰጠው መልስ ይዘትም ባጭሩ፡- አስቀድሞ በመ/ቁ 289197 የነበረው ክርክር ሁከት ይወገድልኝ የሚመለከት ሲሆን አሁን የቀረበው ክርክር መፋለምን የሚመለከት በመሆኑ በሁለቱ መዝገቦች የተያዘው ጭብጥም ሆነ ፍሬጉዳይ የተለያየ በሆነበት በፍርድ ያለቀ ነው ሊባል የሚችል ባለመሆኑ፣ በአመልካች የተነሱት መቃወሚያዎች በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ ተደርገው አመልካች ይዞታው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በስር ፍርድ ቤቶች መወሰኑ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው።

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል።

የግራ ቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ባጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም በሰበር ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዝብ አመልካች ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው በሚል ያቀረቡት መቃወሚያ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ መደረጉ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 5 አተገባበር እና በዚህ ረገድ ሰበር ችሎት ከሰጠው ገዢ የህግ ትርጉም አንጻር መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈፀም አለመፈፀሙን እንደሚከተለው መርምሮታል።

እንደሚታወቀው የመጨረሻ ውሳኔ ስላገኙ ጉዳዮች የሚደነግገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 በንዑስ ቁጥር (1) ላይ በሕግ ስልጣን የተሰጠው ማንኛውም ፍርድ ቤት [illegible] ተቀብሎ የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ተድሞ በፍርድ የተወሰነው ክርክር ሥረ ነገር [illegible] ጭብጥ አንድ ዓይነት ከሆነ በክርክሩ ላይ የነበሩት ወይም ከተከራካሪዎቹ ሙቡት ያገኙ ሶስተኛ ወገኖች [illegible] ሁለተኛ ክስ ወይም ማናቸውንም ዓይነት የፍ/ቤቱን አሰራር ለማቋረጥ አይችሉም በማለት ይደነግጋል።

ሰበር 2
M26T

Scan Me

Scan Me

Scan Me

2:11 pm 05/

CamScanner

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

ሰ/መ/ቁ፡- 263422
ጥቅምት 03 ቀን 2018 ዓ/ም

በመሠረቱ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው ማናቸውም ፍርድ ቤት ታይቶ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ድጋሚ ክስ ሊቀርብበት አይገባም በማለት የተደነገገበት ዋና ዓላማ አንድ ተከራካሪ ወገን በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በተለያየ ጊዜ ክስ እየቀረበበት ጊዜውን እንዳያባክን፤ ተጨማሪ ወጪ እንዳያወጣ እና እንዳይሸማቀቅ ለማድረግ፤ አንድ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በበላይ ፍርድ ቤት እስካልተሻረ ድረስ በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ፤ ክርክሮች በአጭር ጊዜ ውስጥ መቋጫ እንዲኖራቸው ለማድረግ፤ ሕጉ ላልተፈለገበት ዓላማ እንዳይውል በመከላከል የፍትሕ አስተዳደር ሥርዓቱ ተገማች እና ፍትሐዊ እንዲሆን ለማድረግ ስለመሆኑ በዘርፉ ከዳበረው ሥነ ሕግ መገንዘብ ይቻላል።

ስለሆነም አንድ ጉዳይ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ታይቶ ውሳኔ ያገኘ መሆኑ ከተረጋገጠ አዲስ የቀረበውን ክስ በድጋሚ አይቶ ውሳኔ መስጠት ከላይ የተመለከተውን የሥነ ሥርዓት ሕጉን አይነተኛ ዓላማ የማያሳካ እና በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የተጣረሰ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችልበትን ዕድል የሚፈጥር በመሆኑ ፍርድ ቤቶች አዲስ የተረበውን ክስ አስቀድሞ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረበ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 መሰረት ውድቅ ሊያደርጉት የሚችሉት በድንጋጌው የተመለከቱት መስፈርቶች መሟላት አለመሟላታቸው በቅድሚያ ካረጋገጡ በኋላ ነው።

ከክርክሩ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው አስቀድሞ በመ/ቁ 289197 በነበረው የሁከት ይወገድልን ክርክር የአሁኑ አመልካች የዳኝነት ጥያቄ አሁን ክርክር መነሻ የሆነው ስፋቱ 210ካ/ሜ የሆነው ይዞታ ከ1994ዓ/ም ጀምሮ ቤት ሰርቼ እምኖርበት ይዞታዬ ቤቱን አፍርስ በማለት የተጠሪ ተቋም ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት እየፈጠረብኝ ያለው ሁከት ይወገድልኝ በሚል ዳኝነት ሲጠይቁ በወቅቱ ተከሳሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ተቋም ደንብ ማስከበር ጽ/ቤት በሰጠው መልስ አመልካች በይዞታው ላይ መብት የላቸውም፤ ይዞታው የመንግስት መሬት ሲሆን አመልካች በህገወጥ መልኩ ባዶ የሆነን የመንግስት ይዞታ በወረራ የያዙት ሲሆን በ1997ዓ/ምሆነ በ2003ዓ/ም በተነሳው መስመር ካርታ በቦታው ግንባታ አይታይም፤ በቦታው ምንም አይነት ግንባታ የለም፤ በወረራ የያዙት የመንግስት ይዞታ ማስለቀቃችን በህግ የተሰጠን የስራ ሀላፊነት መወጣታችን ከሚያሳይ በቀር ሁከት ተግባር ሊባል ስለማይችል ክሳቸው ውድቅ ሊሆን ይገባል በሚል ተከራክረው ፍ/ቤቱም ለክርክር መነሻ የሆነው ይዞታ በ1997 አየር ካርታ የሚታይ መሆን አለመሆኑ እንዲጣራ በማድረግ የክ/ቀ/የመ/ይ/ስ/ማሳ/ገ//ስራ ሂደት 3454/13፤ በቀን 03/6/2013ዓ.ም በሰጠው ምላሽ ይዞታው አሁን ባዶ ቢሆንም ግንባታው በ1997ዓ/ም በአየር ካርታ የሚታይ መሆኑን ደንብ ማስከበር ተቋም ክስ ከቀረበ በኋላ በይዞታው ላይ የነበረው የአመልካች ግንባታ ያፈረሱ መሆኑ ተረጋግጦ ክርክር ያስነሳው ይዞታ በአሁኑ አመልካች ስር ያለ መሆኑና አግባብ ባለው አካል ሳይፈቀድ የተሰሩ ቦታዎችን ለማስተካከልና ለመከላከል በወጣ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 18/2006 መሰረት በህገ-ወጥ ሰፈራ ይዞታነት ሊስተናገዱ የሚችሉ በመሆኑ የፍ/ቤቱን እንዲፈርስ የሰጠው ማስጠንቀቂያ የማስፈፀም ተግባር የመሆኑ ሁከቱ ሊጠገድ ይገባል እንጂ ፈራሽ መኖሪያ ቤት መነሻ የሆነውን ቤት ጉዳዩ በክርክር ላይ እያለ ማፍረሱ ህገወጥ ተግባር በመሆኑ

Scan Me
Scan Me
Scan Me
CamScanner
2:11 pm 05/

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ስ/መ/ቁ፡- 263422
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጥቅምት 03 ቀን 2018 ዓ/ም

ሊመልስ ይገባል በማለት በነሀሴ 06 ቀን 2013ዓ.ም መወሰኑን የሚያሳይ ነው። በሌላ በኩል ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ በሆነው ጉዳይ በተጠሪ የቀረበው ክስ ይዘት ለክርክር መነሻ የሆነው ይዞታ መሬት ባንክ የገባ የመንግስት ይዞታ ሆኖ እያለ አመልካች በህገወጥ መንገድ በ1997ዓ/ም ሆነ በ2003ዓ/ም በተነሳው መስመር ካርታ ግንባታ የማይታየውን በወረራ በመያዝ ግንባታ የገነባ በመሆኑ ይዞታው መሬት ባንክ የገባ የመንግስት ይዞታ ነው ተብሎ እንዲወሰን እንዲሁም አመልካች በህገወጥ መንገድ የገነባው ግንባታ በማፍረስ ይዞታው እንዲያስረክብ ይወሰንልን የሚል ሆኖ ክርክር ያስነሳው ይዞታ ላይ በ1997ዓ/ም በተነሳው አየር ካርታ ላይ የሚታይ የአመልካች ግንባታ አለ ወይስ የለም? ይዞታ ባለመብት ማነው? የሚለው ጭብጥ ተይዞ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ስለሆነም ቀድሞ በፍርድ የተወሰነው ክርክር ሥረ ነገር እና የተያዘው ጭብጥ አሁን ከቀረበው ጉዳይ ጋር የክሱ ርእስ ልዩነት ያለው ከመሆኑ በቀር የክሶቹ ይዘት፤ የክርክሩ ጭብጥ ተመሳሳይ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

በመሆኑም የሰር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት መወሰን ሲገባው አስቀድሞ የነበረው ክርክር አሁን ከቀረበው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይ የክርክር ጭብጥ ያለው ሆኖ እያለ አመልካች ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ድጋሚ የቀረበ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 ጠቅሶ ያቀረቡት መቃወሚያ በስር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ማጣቱ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 5 አተገባበር አኳያ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 135496፡ በቀን 30/010/2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ብይን በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 312040፡ በቀን 30/07/2016 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ስነ- ስርኣት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽሯል።
2. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት የተጠሪ ክስ አስቀድሞ ፍርድ ባገኘ ጉዳይ በድጋሚ የቀረበ ነው በማለት ወስነናል።
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ።

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል።

ሰበር 2